# «ውህደት ለተሻለ ውጤት»



**የሴክተሩ ባለሙያዎች በ(BPR) ጥናት ላይ**

በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች ህዝቦች ክልል መስተዳድር የመሰረታዊ የስራ ሂደት ለውጥ ጥናትና ትግበራ በሁለት ዙር መካሄዱ ይታወቃል።

ለሙከራ ይረዳ ዘንድ ታስቦ በመጀመሪያ በ7 የመንግስት መስሪያ ቤቶች ብቻ የተካሄደ ሲሆን ሁለተኛው ዙር የBPR ትግበራ ግን በአጠቃላይ በክልል የሚገኙ ቀሪ የመንግስት መ/ቤቶችን ያካተተ ነው።

የክልሉ ገቢዎች ባለስልጣንም በዚህ በ2ኛው ዙር የመሰረታዊ የስራ ሂደት ለውጥ ጥናት ተከትሎ ወደ ሙሉ ትግበራ ገብቷል።

በመሆኑም የተበታተኑና ተመሳሳይነት ያላቸው ልዩ ልዩ ስራዎች ተለይተውና ተመዝነው በአንድ ማዕከል እንዲከናወኑ የሚያስችል አገልግሎት አሰጣጥን በማፋጠን የተገልጋዩን የአገልግሎት ዕርካታ ግምት ውስጥ ያስገባ ጥናት እንዲካሄድ ተደርጓል።

በዚሁ መሰረት ከዚህ ቀደም የነበሩ የባለስልጣኑ አደረጃጀት ከአገልግሎት አሰጣጥና ፍጥነት አንፃር ተፈትሸው ተመሳሳይነት ያላቸውን ስራዎች በአንድ የስራ ሂደት እንዲጠቃለሉ በመደረጉ 3 ዋና የስራ ሂደትና 7 ደጋፊ የስራ ሂደቶች ብቻ ተደራጅተው የአገልግሎት አሰጣጡን ቀልጣፋና ፍትሀዊ በማድረግ አበረታች ውጤት እያስመዘገበ ይገኛል።

የገቢ አሰባሰቡ ስርዓት አንድ ወጥ ይሆን ዘንድ ቀድሞ በስራና ከተማ ልማት ቢሮ ስር የከተሞች ገቢ በጀትና ሂሳብ ዋና የስራ ሂደት በኩል ይከናወኑ የነበሩ የገቢ ጥናትና አሰባሰብ ስራዎች በገቢዎች ባለስልጣን በኩል እንዲከናወኑ መደረጉም ሌላው የመሰረታዊ የስራ ሂደት ለውጥ ጥናቱ ያመጣው ውጤት ነው::

በአንድ አስተዳደራዊ እርከን ውስጥ በሁለት የተለያዩ መ/ቤቶች ይከናወን የነበረውን ተመሳሳይ ተግባራት ወደ አንድ መ/ቤት በመሰብሰብ፤ አገልግሎትን በአንድ ቦታ በቅርብ ርቀት በመስጠት የተገልጋይ ህብረተሰብን እንግልት ጊዜና ገንዘብ በመቀነስ መልካም አስተዳደር ለመፍጠር አስተዋፅኦ እያበረከተ ይገኛል::

ከዚህም ሌላ ውህደቱ ለተሻለ ውጤት በመሆኑ መንግስት ተግባራቱን ለማከናወን በተለያዩ ሁለት መ/ቤቶች ይመደብ የነበረውን የሰው፣ የገንዘብ እና የማቴሪያል ሀብት በአንድ መ/ቤት በመጠቅለል ያለአግባብ ይባክን የነበረውን የሰው፣ የገንዘብና የማቴሪያል ሀብት ለተለያዩ የልማት ተግባራት እንዲውል ምቹ ሁኔታ ፈጥሯል::

ውህደቱ በከተሞች ፣የበጀት የክፍያና ሂሳብ ስራ ወደ ፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ጽ/ቤት፣ የገቢ ጥናትና አሰባሰብ ስራ ወደ ገቢዎች አስተዳደር ጽ/ቤት እንዲሆን የተደረገው የከተሞች ፋይናንስ የሚመራበትን ስርዓት ለመወሰን የወጣውን ደንብ ቁጥር «70/2000«ን እና የተለያዩ መ/ቤቶች ስልጣንና ተግባር ለመወሰን የወጣውን አዋጅ ቁጥር «127/2002»ን የህግ መሰረት ተከትሎ የተፈፀመ ነው::

ይህ ውህደት ከገቢ አሰባሰብም ሆነ ከአገልግሎት አሰጣጥ አንፃር ለተሻለ ውጤት ከመሆኑም በላይ ከክልል ጀምሮ በተዋረድ እስከ ክፍለ ከተማ የተደረገው የውህደት ስራ በቀጣይ በሌሎች የወረዳ እና የመዘጋጃ ቤት መዋቅሮችም ለመቀጠል በፋይ/ኢ/ል/ቢሮ እና ገቢዎች ባለስልጣን ደረጃ የተለያዩ ጥናቶች በመደረግ ላይ ሲሆኑ ጥናቱን መነሻ በማድረግም በክልል ካብኔ ውሳኔ ያገኛል ተብሎ ይጠበቃል::

ስለዚህ ይህ ውጤታማ ተግባር ተጠናክሮ እንዲቀጥል የሁሉንም ተገልጋይ እና ባለድርሻ አካላት ቅን ትብብርና ያለሰለሰ ድጋፍ ይሻል::